# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 42 የካቲት 26 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

...በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ስርአት ያልተበደለ ብሄረሰብ አለ እንዴ ? ያልተረገጠ ማንነቱን እስኪረሳ ድረስ እነሱ በመረጧቸው አፈ ጮሌዎች እንደፈለገ ሲደረግ ያልቆየ የህብረተሰብ ክፍል አለ እንዴ? ትግራይን ጨምሮ?...

## የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከአሜሪካን ድምጽ ሬዴዮ ጋር ያደርጉት ቃል ምልልስ


**በገጽ 3 ላይ ይመልከቱ**


## ጻረ-ወያኔ አለማቀፍ ትእይንተ ህዝብ በአለም ታላላቅ ከተሞች ተደርጎ ዋለ

መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ በህዝባችን ላይ እያደረሱት ያለውን ሰቆቃ በመቃወም በተለይም ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ በመሄድ ላይ ያለዉን ከፍተኛ የመብት ረገጣ፤ አፈና እና ሀገር የመሸጥ ወንጀል በመቃወም፣ በተለያዩ ምክንያቶች ከእናት አገሩ ወጥቶ ውጭ የሚኖረውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ያሰባሰበ ትዕይነተ ህዝብ ባሳለፍነው ሰኞ የካቲት 23 ቀን በታላላቅ የአውሮጳ፣ የሰሜን አሜሪካና አውስትራሊያ ከተሞች መካሄዱን የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢዎች ሰላማዊ ሰልፉ ከተካሄደባቸው አግሮች ዘገቡ።

የሰላማዊ ሰልፉ አዘጋጅ የሆነው "አለም አቀፍ ለፍትህና ለሰብዓዊ መብት በኢትዮጵያ አስተባባሪ ኮሚቴ" በሰጠው ዘገባ የሰልፉ ዋንኛ አላማ፣ በአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲያብብ ነጻ ተቋማት እንዲፈጠሩ በመጠየቋ የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን፤ ስለ ፍቅር፣ ሰላም፣ መቻቻል እና አንድነት ማቀንቀን ወንጀል ሆኖ በእስር የሚማቅቀውን አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁንን ወይም ቴዲ አፍሮንና በተለያዩ ጊዜያት በመለስ አገዛዝ እየታፈኑ በተለያዩ እስር ቤቶችና ማጎሪያ ጣቢያዎች የሚማቅቁ የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ለመጠየቅ እንዲሁም የአገራችን ለም መሬት ለጎረቤት ሱዳን አሳልፎ መስጠቱን ለመቃወም እንደሆነ ታውቆአል።


**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**


## የግንቦት 7 ንቅናቄ በጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ አደረገ

ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ባለፈው ቅዳሜ የካቲት 21 በጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ ላይ ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ የንቅናቄው ከፍተኛ አመራር አካል በሆኑት በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የተመራ ሲሆን በበርካታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ በተሳካ ሁኔታ የተካሄደ እንደነበር ዘጋቢያችን ከስፍራው ዘግቧል።

በስብሰባው ላይ አቶ አንዳርጋቸው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ከዳሰሱ በኋላ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ አኳያ የተቋቋመበትን ዋና አላማ ያስተዋወቁ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ ከተሰብሳቢዎች በተነሱላቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ላይም በመመርኮዝ ገንቢ ውይይት መካሄዱን ከዘገባው ለማወቅ ተችሏል።


**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**


ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የአድዋ ድልን 113ኛ አመት መዘከር

በዚህ ሳምንት የአድዋ ድልን 113ኛ አመት እንዘክራለን ። የተለያዩ ሃገራት ህዝቦች ተመሳሳይ ክብረ በአላትን ያከብራሉ ። ምክንያትም አላቸው ። የታሪካቸውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣ ባለፈው የድል ታሪካቸው ለመኩራትና፣ ሊደግሙት እንደሚችሉም ለአዲሱ ትውልድ ለማስተማር፣ የአያቶቻቸውን ጀግንነት ለማውሳት፣ ከየት ጀምረው የት እንደደረሱ እንደ ታሪካዊ ክንዋኔ ርቀት መለኪያ ደንጊያም ይጠቀሙበታል ። በተለይ ለኛ ለኢትዮጵያውያን፣ አንድን የአውሮፓ ሃይል ሰብረን አለምን ጉድ አሰኝተን፣ በቅኝ አገዛዝ ለወደቁ ህዝቦች ደግሞ የአርነት ተምሳሌት ለነበርንና፣ ዛሬ የድል ተደራጊዎቹ ተመፅዋቾች፣ የአፍሪካውያንም ማፈሪያ ከመሆን ደረጃ እንዴት እንደደደረስን ጓዳችንን ለመፈተሻ ብንጠቀምበት ተገቢ እንጂ ነው ። ለምን አድዋ ላይ ድል ተቀዳጀን? ከድላችንስ ምን ተማርን? እንዴትስ ቢሆን ካለንበት መቀመቅ ልንወርድ በቃን?

ዘመኑ አውራ ምሁር ከነበሩት ዋነኛው አፈወርቅ ገብረየሱስ ዘብሄረ ዘጌ ልክ የዛሬ 100 አመት በ1901 አም ባሳተሙት "ዳግማዊ አጤ ምኒልክ" በተሰኘው መፅሃፋቸው "ዳግማዊ ምኒልክንስ እግዚአብሄር መርጦ፣ ሂድ ኢትዮጵያ ተጎድታለች፣ የኢትዮጵያ ሰው አልቅሷል፣ በህዝቡ ድንቁርና በዝቶበታልና፣ ሂድ ኢትዮጵያን አይዞሽ በላት፣ የድሃውን እንባ አድርቅለት፣ ድንቁርና ጨለማ፣ እውቀት ግን ብርሃን ነውና፣ በኢትዮጵያ ጨለማው እንዲሻር፣ ብርሃን እንዲወጣ፣ ለህዝቡ የረቀቀው በልብ፣ የጎላው በዐይን እንዲከሰትለት አስተምረው፣ አርመው፣ ጠብቀው፣ ላንተ አይደለም፣ ለኢትዮጵያ ነው ያነገስሁህ ብሎ ላከው ።" በማለት የምኒልክ አመራር ከደቡብ እስከሰሜን ያለውን ህዝብ እንዴት አድርጎ በወራሪው ጠላት ላይ እንዳሰለፈው ዘግበዋል ። ከአድዋ መልስ ባሉ 113 አመታት የመሪነቱን መንበር ስለተቀመጡበት አምባገነኖች ግን በተመሳሳይ ልበ ሙሉነት "ለኢትዮጵያ ነው የነገሱት ለነርሱ አይደለም" ብለን ለመናገር አለመቻላችን፣ ዛሬ ለምንገኝበት መቀመቅ ታላቁን አስተዋፅኦ ያደረገ ይመስለኛል ።

የአፈወርቅ ገብረየሱስ የምኒልክ አመራር ከሌሎቹ ቀደምቶቹ ነገስታት እንዴት ይለይ እንደነበር ሲያወሱም "እስከ ትላንት ድረስ፣ በነቴዎድሮስና በናፄ ዮሃንስ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ድሃ ለወታደር መጫወቻ፣ ባርያ ነበር ። ባርያ በገዛ ራሱ ማዘዝ እንደማይሆንለት፣ የኢትዮጵያ ድሃም፣ በገዛ ቤቱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበረ ። የሚአዝበት፣ ቆርፋፋ ጋሻ ያነገበና፣ አንድ ባለጌ ጦር የያዘ፣ አንድ የመሸበት፣ ደበናንሳ የጀራረገውና፣ ተሰገባው በስፋራ ተጣልቶ ፀሐይ የሚሞቀው ጎራዴ መሳይ በወገቡ ያገነበጠ፣ ቅማላም ወታደር ነበረ ። ይሄው ወታደር፣ እንኳንስ ተሰሪነት ገብቶ፣ ለቅሉጥ ሄዶም ባደረበት አገር ሳይቀር፣ ደሀውን የፊጥኝ አስሮ፣ ነጭ ኑግ፣ ጥቁር ወተት ውለድ ሲልና፣ ባለቤቶቹ፣ ምሽቲቱ እንደገረድ፣ ባልዬው እንደሎሌ፣ እግር አጥበው፣ አልጋ አንጥፈው፣ ትራፊውን በልተው፣ እነሱ ተምድር፣ እሱ ታልጋ ተኝተው ያድሩ ነበረ ። ... የውነት ነው፣ እንዲህ ያለውን ስራ፣ እነዚያ ንጉሶች አድርጉ ብለው አልነበረም፣ ነገር ግን፣ በነዚአ ንጉሶች ጊዜ ማን ደፍሮ ከወታደር ጋራ ይናገር ነበረ፣ ለነዚያ ንጉሶች የበህር ልዣቸው ወታደር ብቻ ነበረ ። ባላገሩንማ እንደ እንጨት ጠርበው፣ እንደ ጭቃ አንቦልቡለው የሰሩት ያስመስሉት ነበር እንጂ፣ እንደነሱ በአርአያ ስላሴ የተፈጠረ አይመስላቸውም ነበረ ።...አሁን በደጉ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ግን ያ ሁሉ መከራ፣ ያ ሁሉ ግፍ ቀረ፣ በኢትዮጵያ ፀሐይ ወጣ ጨለማ ተሻረ፣ ወታደርና ባላገር፣ ትክክል ያድር ጀመረ፣ ደሀና ባለጠጋ ትክክል ተናግሮ፣ ሁሉም እንደልቡ ተዛንቶ ይኖር ጀመረ ፤ አለፈለት ደስ አለው፣ በዓለም እንቅልፉን ይተኛ ጀመረ ።" ዛሬም የኢትዮጵአ አበሳ፣ አፈወርቅ ከምኒልክ በፊት ነበር የሚሉት የወታደር የበህር ልጅነት የሰፈነባትና፣ ዛሬም እንደ 113 አመታት በፊቱ ህዝቡ "የቅማላም ወታደር" መጫወቻ መሆኑ ።

የጣሊያን ወረራ ከዚህ መልካም እንቅልፉ ሲቀሰቅሰው፣ የኢትዮጵያ ድሃና ባለጠጋ "እምቢ ለኢትዮጵያዬ"ን ፈከረ ። የአድዋ ድልም ምስጢር ይሄው ነው ። ለታሪካዊ ወቅቱ የሚመጥን አመራር የህዝቡን አቅምና ተነሳሽነት አስተባብሮ ተአምር መከወን የመቻሉ ሃቅ ። ስለ አድዋ ጦርነትም አፈወርቅ ሲዘግቡ "የኢትዮጵያ ጦር ወደ አዲ የተጓዘ ጊዜ፣ ከዳጋሙስ ተነስቶ ወደ አዲ ትይዩ ተጓዘ ። የዚህን ጊዜ ከጣልያኖች ጋር የነበሩት ያጋሜ ገዢዎች እነራስ ስብሃት፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት እንደገነገነ፣ የኢጣልያ ጦር እንደመነመነ ተጋፍቶ እንዳይጋፋ አዩትና፣ ከድተው ብዙ የኢጣልያ ሰው ፈጅተው፣ ላጤ ምኒልክ ገቡ ። ከዚህ ወዲያ የኢጣልያ ጦር ቅስሙ መሰበር ጀመረ፤ ካንዱ ስፍራ ወዳንዱ ስንቅ መቀባበል የማይሆንለት ሆነ ። ... የኢጣልያ መንግስት... የነገሩን መክበድ ባየው ጊዜ፣ ብዙ ጦር ታገሩ አዘዘና፣ የፊት ፊቱን እንደተሰናዳለት ይሰድ ጀመረ ። አሳቡ ግን የበቃውን ያህል ጦር ለመስደድ ነበረ ። በዚህ መካከል ገና ሶስት እልፍ ወታደር ከሙቶ መድፍ ጋራ፣ ባልዲሴራ የሚባል አንድ ጀነራል ከሁሉ በላይ ሹሞ ሰደደ ።


**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

# ርእሰ አንቀጽ

## እውን ዴሞክራሲ ሂደት ሆኖ ነው በሃገራችን መስፈን ያቃተው፣ ወይስ

ዴሞክራሲ ዛሬ በዳበረበት መልኩ በሰፈነባቸው ሃገሮች ብዙ ዘመን የፈጀ መሆኑን አንስተውም:: በግሪኳ አቴና የተሞከረውን የዛሬ 2500 አመት በፊት የነበረውን እንኳን ብንተወው፣ የዴሞክራሲ ስርአት ራሱን አሁን በምናያበት መልኩ ለመከሰት ወደ 500 አመታት ወስዶበታል:: የሚገርመው ግን ይህ የዴሞክራሲ ጉዞ ሁሌ እንደሚነገረን 500 አመት የፈጀው የዘመናች ዴሞክራሲ ማህጸን በሆነችው ታላቂቷ ብሪታንያ ውስጥ የሚኖረው ህዝብ የዴሞክራሲ እሴቶች የማይገባው፣ እድሉ ቢሰጠው አጠቃቀሙን የማያውቅ፣ እንዳውም አልፈልግም ብሎ ያስቸግር ስለነበረ አልነበረም::ምክንያቱም የዴሞክራሲ መሰረታዊ እሴቶች ነጻነት፣ አኩልነት፣ የማንም እቃና ባርያ አለመሆን የሰው ልጅ በሰውነቱ ይችን ምድር ከረገጠበት ጀምሮ አብሮት ያለ የማንም አስተማሪነትና ስብከት የሚፈለግ ጉዳይ አይደለምና::

ዴሞክራሲው ጊዜ የፈጀው፣ ፈጣሪ በሰው ልጆች ነፍስ ላይ ያተመውን የነጻነት ውበት የእንግሊዝ ጭሰኛ ስላልገባው፣ የእንግሊዝ ሴቶች እኩልነትንና ነጻነትን ከማማሰያና ከምጣድ ለይተው ማየት ባለመቻላቸው አልነበረም:: የእንግሊዝ ነገስታትና መሳፍንቶች ከራሳቸው ጥቅም ተነስተው ገበሬና ሴት፣ መሬትና ቤት የሌለው ፖለቲካ አይገባውም፣ ሃላፊነት አይሰማውም፣ ምድቡ ከእንስሳ ወይም ከእቃ ነው ብለው ለመቶ አመታት ፓርላማ በራፍ ድርሽ እንዳይል ባያደርጉት ኖሮ ዴሞክራሲ በአለማችንን ለማበብ ያንን ያህል ዘመን አይፈጅበትም ነበር:: በታላቋ የዘመናችን ዴሞክራሲ በአሜሪካ የጥቁር ወንድሞቻችን የፖለቲካ መብት እስከ ዛሬ ሃምሳ አመት በፊት ድረስ መከበር ያልቻለው፣ ዛሬ ግን በእዚህ አጭር ግዜ ውስጥ፣ በስነ ስርአት የድምጽ መስጫ ወረቀት ሳጥን ውስጥ መጨመር አይችሉም ተብለው የነበሩ “ግኡዞች” ከመሃላቸው የታላቋ ዴሞክራሲ የአሜሪካ ፕሬዚደንት የሆነ ልጃቸውን፣ ባራክ ኦባማን ለክብር ያበቁት፣ ሚስጥራዊ የዴሞክራሲ ብስለት በብርሃን ፍጥነት በመላበሳቸው አይደለም::

ዛሬ ዴሞክራሲውን የሚደግፉ ተቋማት የተተከሉባቸው ህንጻዎች፣ ለዜጎች መረጃና ዜና የሚቀርብባቸው መሳሪያዎች ግዜ ወሳጅ፣ በሂደት የመጡ ናቸው:: ይህ ማለት ግን ህዝብ ሁሉ በሰማይ ጠቀስ ፎቅ ካልኖረ፣ በካዲላክ ካልፈሰሰ፣ ምግብ ተርፎት ባህር ውስጥ ካልደፋ፣ የሚያስተዳድሩትን መምረጥ፣ በነጻ ለመተንፈስ፣ በእኩልነት ለመዳኘት ፍላጎት የለውም ማለት አይደለም::

ለእዚህ ነው የኢትዮጵያ ገበሬ በባዶ ሆዱ፣ መጨቅጨቂቱን እንደለበሰ ኩኬው አስከሚንቀጠቀጥ ለሰአታት ቁሞ በምርጫ 97 ደምጹን በምርጫ ኮሮጆ ውስጥ የጨመረው:: ነጻነት አኩልነት ፍትህን የመሰሉ እሴቶች፣ የአቴና ዴሞክራሲ ሲሞላቀቅበት ለነበረው፣ ከባለሃብቶቹ ቁጥር ይበልጥ ለነበረው ባሪያ ትረጉም ነበረው:: ኋላም በ1950ዎቹም 2500 አመት በፊት ከነበሩ የአቴና ባሪያዎች ልዩነት ባልነበረው መንገድ ሲታዩ ለነበሩ አፍሪቃዊ አሜሪካውያን ተመሳሰይ ትርጉም ነበረው:: በ1997 አ.ም በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ግፉአንም ትርጉም የነበረው፣ የሰው ልጅነት ትርጉሙ ከነጻነት የማይለይ፣ ከእኩልነትና ከፍትህ ተነጥሎ የማይታይ ስለሆነ ብቻ ነው::

በኢትየጵያችን የነገሱት አምባገነኖች ዴሞክራሲ በብዙ ሃገሮች በመቶዎች የሚቆጠሩ አመታት ፈጅቷል ሲሉን የእንግሊዝንና የአሜሪካንን ታሪክ እያየን እንድንሞኝላቸው በማሰብ ነው:: እውነቱ ግን የዴሞክራሲ ግንባታው ብዙ መቶ አመታት ፈጅቷል በሚሉባቸወ ሃገሮች ውስጥ የግንባታው ግዜ ከሚገባው በላይ የተራዘመው ህዝብ ዴሞክራሲ ስለማይጥመው ወይም የነበረው የማህበራዊና የኢኮኖሚ ደረጃ፣ ሰዎች እራሳቸውን ያስተዳድሩ ወይም አስተዳዳሪዎቻቸውን ይምረጡ ቢባል ሰርአቱን ሊሸከም ባለመቻሉ አልነበረም:: በዋነኛነት ዴሞክራሲን ረጅም ሂደት ያደረገው ዴሞክራሲ ከስልጣናቸውና ከጥቅማቸው እንደሚነቅላቸው የሚያውቁ፣ ይህንን ስልጣንና ጥቅም ለመከላከል ሲሉ ባደራጁት የጦር ሃይል፣ ነጭ ለባሽና ምስለኔ የአውሮፓን ጭሰኛና ሰራተኛ የአሜሪካንን አፍሪቃዊ ሴቱንና ወጣቱን አፍነውና ረግጠው ለመግዛት ፍላጎቱ የነበራቸው ገዥዎች ስለነበሩ ብቻ ነው:: የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የገጠመው ፈተናም ይኸው ነው::

በሃገችንም በተለይ በእዚህ ዘመን፣ በተለይ ከዴሞክራሲ አዝጋሚ የታሪክ ሚስጠር ለምን ግዜ እንደፈጀ በሚገባ ከተረዳን በኋላ የህዝብና የተቃዋሚዎች ችግር ዴሞክራሲ ሂደት መሆኑን ካለማወቅ የሚመጣ ነው የሚለውን ቅጥፈት ከአምባገነኑ መለስ ዜናዊ እንሰማለን:: ይህንንም የሂደት ጨኸት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲያስተጋቡት ይደመጣል:: በእዚህ ላይ ደግሞ የሚገርመው የምእራብ መንግስታት የራሳቸውን ታሪክ እያጣቀሱ የመለስ ዜናዊን አይን ያወጣ ዘረኛ አገዛዝ እንደ ዴሞክራሲ ግንባታ ሂደትነት የማጭበርብር ማስመሰሉን በገድል ማሚቶነት ያስተጋባሉ::

ጥያቄው ግን ኢትዮጵያውያን በምርጫ 97 ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ያሳዩት ትጋትና የከፈሉት መስዋእትነት እርባና አጥቶ የቀረው፣ ዛሬ ሃገራችን በግንቦት 97 ምርጫ ደርሳበት ከነበረው አዲስ የአብርሆት ዘመን ተመልሳ ተንሸራታ ወደ ጨለማ ዘመን የወደቀቸው የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ስለሆነ፣ ወይስ መለስ ዘረኛና አምባገነናዊ የበላይነቱን ለማስጠበቅ ሲል፣ ምእራባውያንም መለስ ለጸረ ሽብርተኛነት ጦርነት ይጠቅመናል በሚል ስሌት ዴሞክራሲን መፈንግጡን የሚገድለውን ገድሎ የሚያስረውን አስሮ በስልጣን መቆየቱን ሰለመረጡት?

የሃገሩ ገዠዎች ዋነኛው የዴሞክራሲ ጠላቶች በሆኑበት ሃገር የ“ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ነው” የማለት መብት የላቸውም:: የሌባ አይነ ደረቅ የሚያደርጋቸውም ይህ ድርቅናቸው ነው:: በምርጫ 97 እንደታየውም ህዝብ ለዴሞክራሲ መስፈን ብቃቱን ሲያሳይ ይህንን ብቃት የሚመጥን የዴሞክራሲያዊነት ስብእና መላበስ ያልቻሉት ኋላ ቀር የሃገሪቱ ገዥዎች ናቸው:: ይህን ካየን በኋላ ዴሞክራሲ ሂደት ነው ሲባል የሚገባን አንድ ነገር ብቻ መሆን አለበት::

ይህ ሂደት መለስን የመሰሉትን የዴሞክራሲ ደንቃራዎች ጠርጎ የሚያልፍ ሂደት መሆኑን ብቻ::

## ጸረ-ወያኔ አለማቀፍ ... ( ከገጽ 1 የዞረ)

በዚሁ መሠረት ሰላማዊ ሰልፈኞቹ የወቅቱን ከፍተኛ ብርድ በመቋቋም በዋሽንግተን ዲሲ የስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊት፤ በሎንደን፤ በሙኒክ፤ በፍራንክፈርት፤ በበርን፤ በኦስሎ፤ በስቶክሆልም፤ በሮምና በሜልበርን አውስትራሊያ ከአሜሪካ ኤምባሲ ጽ/ቤቶች ፊት ለፊት ደማቅ ትዕይነተ ህዝብ ማድረጋቸው ተዘግቦአል።

የግንቦት 7 ሬድዮ ሪፖርተር ከዋሽንግተን ዲሲ እንደዘገበው በእለቱ የነበረው በረዶና ቅዝቃዜ እጅግ አዳጋች ቢሆንም ሰልፈኞቹ ያንን ተቋቁመው ቁጣቸውን ሲገልጹ ነበር ብሏል። ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው አንድ የሰልፉ ተሳታፊ የነበረውን ሁኔታ ሲገልጹ፤ “እኔ ከአገሬ ከተሰደድኩ አራተኛ አመቴ ነው። የቅንጅት መሪዎች በታሰሩበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ሰልፍ ወጥቼ አውቃለሁ። እኔ በዚህ አገር በቆየሁባቸው በእነዚህ አመታት እንዲህ አይነት በረዶ ሲወርድና እንደዛሬ አይነት ቅዝቃዜ ተሰምቶኝ አላውቅም። ነገር ግን በአገራችን ያለው ሁኔታ ይህን ሁሉ ተቋቁመንና የሚቻለንን ሁሉ አድርገን የመለስን አገዛዝ እንዲወገድ እንድንረባረብ የሚያደርገን ስለሆነ እንጂ የዛሬስ ቅዝቃዜና ብርድ የሚቻል አልነበረም” ብለዋል።

ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው ሌላ ሰልፈኛ ደግሞ፣ “በእርግጥ ቅዝቃዜው ፈታኝ ነው፤ ነገር ግን ለነጻነት የሚደረግ ትግል ከዚህም የከፋ መስዋዕትነት ያስከፍላልና አገራችን የዜጎቿ መብት የተከበረባት ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት እስክትሆን ድረስ ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ መክፈል የግድ ይላል። መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ አገራችንን ሲያጠፉ እያየን ለስጋችን ምቾት የምንጨነቅ አለመሆናችንን ልናሳያቸው ይገባል። ይህ ልናበረክተው ከተነሳንለት ሁለገብ ትግል ዋጋ አኳያ ኢምንት ነው። ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ነጻነት እንዲሁ በዋዛ የተገኘበት የምድራችን ክፍል የለምና” ብለዋል ።

## የግንቦት 7 ንቅናቄ ... ( ከገጽ 1 የዞረ)

በዚሁ ለአራት ሰአታት በቆየ ስብሰባ አቶ አንዳርጋቸው እንደ መዥገር በሃገራችን ላይ ተጣብቀው ደሟን እየመጠጡ ያሉትን የነመለስን የወንበዴ ቡድን አሽቀንጥሮ ለመጣል የሚደረገው ትግል ምን መምሰል እንዳለበትና አላማውም ምን መሆን እንዳለበት በሰፊው የተነተኑ ሲሆን፣ ለተግባራዊነቱም ምን መደረግ እንዳለበትና ከያንዳንዱም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ምን እንደሚጠበቅ አብራርተዋል። ተሰብሳቢዎቹም በቀረቡት ግልጽ ማብራሪያዎችና ለቀረቡት ጥያቄዎች በተሰጡት ምላሾች መደሰታቸውን የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ይህንንም እርካታቸውን በስብሰባው መጨረሻ ላይ በተደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ መግለፃቸውን ዘግቧል።

በስብሰባው ላይ ለመገኘት በርካታ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ የጀርመን ከተሞች እና ከሆላንድ፣ ከሲውዘርላንድ፣ ከኦውስትሪያ ረዥም ርቀት ተጉዘው መምጣታቸውን ዘጋቢያችን አያይዞ ገልጾልናል።

## የአድዋ ድልን .... (ከገጽ 1 የዞረ)

ጀነራል ባራቴሪ፣ እስከዛሬ እንዲህ ማስኘ፣ ክብር በማገኝበት ጊዜ እንዲህ ሌላ በላየ ተሹሞ፣ እኔ በታች ልሆንና፣ ድልም ብናደርግ፣ ክብሩ ሞገሱ ለሱ ሊሆን? እገጥማለሁ ብሎ ቅዳሜ ማታ በሚአዝአ በሁለት ቀን ወደ አዷ ሌሊቱን ሲገሰግስ አደረ ። ...ያ ሁሉ ፈረንጅ፣ ያ ሁሉ ጎበዝ፣ ያ ሁሉ ወጣት ልዥ በአገሩ እንዲአ ሲአምርበት፣ በሰው አገር ላሊበላ ሳሚ መስሎ፣ ኮርፈፍ ኮርፈፍ ሲል፣ ታገሩ ወጥቶ ተናቱ ተላቅሶ፣ ከወላጆቹ ተሳስሞ፣ ተጌትነቱ፣ ከደስታው፣ ታገሩ ተወንዞ ተነጥሎ፣ ወዙን በግምባሩ እያንጠበጠበ፣ በረሃብ ጎኑ ተጣግቶ፣ በጥማት ልሳኑ ታስሮ፣ ሲማስን ሲደክም ሲንደላቀፍ አድሮ ሳያርፍ፣ ወዙን ሳያደርቅ ሲነጋጋ አባ ገሪማ ደረሰና መድፉን ጠመደ፣ ገና ቃታው ከደረቱ ሲዘልበት የጠበንጃውን ቃታ ከፈተ፣ ጦርነት ተጀመረ ። ከዚአማ ወዲአ ምን ያነጋግራል፣ አሞራው ሸዌ አዳጋ እንደተጣለበት ባየ ጊዜ፣ የቸኮለ በሌጣው ያልቸኮለም በኮርቻው እየተሰካ፣ እየፈከረ፣ እየተንደቀደቀ ገባበት ።....እንደውነት ግን ፊት የደረሰው የኢጣልያ ጦር አሳምሮ ተዋጋ፣ በወተድሲ እያንገበገበ አንዱን ወገን ሰበረና፣ እየተከተለ ተመሃል ገባ ።

(ወደ 4 ገጽ ዞሯል)



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከአሜሪካን ሬዴዮ የዲሞክራሲ ክፍል አዘጋጅ ትዝታ በላቸው ጋር ያደርጉት ቃል ምልልስ

**ቪኦዔ፣** አጠር አድርገው የግንቦት7ን ዋን አላማ ያስረዱን እስቲ?

**ዶር ብርሃኑ፣** የግንቦት 7 ዋና አላማ በጣም ቀላላና በጣም ግልጽ ነው፥ እኛ በመሰረቱ ከግንቦት 97 ምርጫ በኋላ በስልጣን ላይ ያለው የነመለስና የነበረከት ቡድን ህገወጥና በጉልበት ስልጣን ከህዝቡ አፍኖ የተቀመጠ በምንም የሞራልና የህግ መለኪያ በስልጣን ላይ መቆየት የማይችልና የሌለበት ለዚህም ማህበረሰቡ እንዲህ አይነቱን ስልጣን በሃይል የያዝ ቡድን በምንም መልኩ ታግሎ መጣል ስባዊም ተፈጥሮአዊም ነው ብለን እናምናለን እና ይሄንን ተግባራዊ ለማድረግ የተመሰረተ ድርጅት ነው በራሱም ሆነ ከሌሎች ጋር ተባብሮ ለዛ የሚሰራ ቡድን ነው ድርጅታችን

**ቪኦዔ፣** ዶር ብርሃኑ እንግዲህ ድርጅተዎ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሁሉንም የትግል ዘዴ እንደሚጠቅም በተደጋጋሚ በመግለጫችሁ ተመልክቷል ኢህአዴግን ስልጣን ለማስለቀቅ የመሳሪያ ትግል እንዳንድ አማራጭ የምትውስዱት ነው ማለት ነው?

**ዶር ብርሃኑ፣** ኢህአዴግን ለማስወገድ የመሳሪያ ትግል የጀመሩ ሀይሎች ቅደም ብሎ እንዳሉ ይታውቃል እኛ ምርጫ 97 በፊት ኢህአዴግን ከዚህ ከጉልበትና ከአመጽ መንገዱ ተመልሶ የህዝብን ውሳኔ ለመቀበል ይችል እንደሆን ብለን በሰፊው የሞከርን ሰዎች ነን ግንቦት7ን ያቋቋምነው የህዝቡን ምርጫ መዝረፍ ብቻ አይደለም ለምን ትዘርፋለህ ብሎ በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም የወጣውን ግንባር ግንባሩን ቆልቶ የጨረሰ ቡድን ነው ስለዚህ በሞራልም በምንም መለኪያ ስልጣን ላይ መቆየን የሌለበት ነው ብለን ስለምናምን ይሄንን ደግሞ በምንም መልክ ለመጣል የሚደረግ ትግል ፍትሃዊና በሞራልም መንገድ ተቀባይነት ያለው ነው ብለን ስለምናምን ይህንን መንግስት ለመጣል ይጠቅማል የምንለውን ህዝቡን በተለይ የማይጎዳ እስከሆን ድረስ ማንኛውንም የትግል ስልት መጠቀም አለብን እኛን ብቻ ሳይሆን ይህንን የሚጠቀሙ ሃይሎችም በሞራል በኩል ተቀባይነት አላቸው ብለን ነው የተነሳነው

**ቪኦዔ ፣** ውደኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ቅንጅት ላንድነትና ለዲሞክራሲ 97ቱ ምርጫ ሲላተፍ የውስጥ መናቆር እንደነበረበትና እንደ ድርጅት ጠንካራ እንዳልነበር እንዲሁም ደግሞ ብቂ የሰላማዊ ትግል እንዳልተደረገ የሚተቹ አሉ ከዚህ አንጻር ሰላማዊ ትገል ገና አልተነካም በሰላማዊ ትግል መቀጠል አስፈላጊ ነው የሚሉ አሉና የርሶ መልስ ምንድን ነው?

**ዶር ብርሃኑ፣** በምንም መልኩ አንድን ኢህጋዊና ጉልበተኛ መንግስት የህዝቡን ነጻነት ወደሚያከብር ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመለወጥ በሰላማዊ መንገድ እስከተቻለ ድረስና እና ሰላማዊ መንገድ እስከሰራ ድረስ ሁሌም የሚመረጠው እሱ ነው ሰላማዊ መንገድ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ታምኖ ወይም ቢያንስ እንዳው ከፍተኛ ሊሆን የሚችልበት እድል አለ ተብሎ ታምኖ ወደሌላ ትንሽም ቢሆን ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መንገድ መሄድ ትክክል አይሆንም:: እኛ እዚህ ደርጃ ላይ የደረስነው ያ መንገድ አያስኬድም ውጤት አያመጣም ብለን ስላመንን ነው ይህን ያመንበትን ምክንያት ደግሞ ሰላማዊ መንገድ በታሪክ በሌሎች አገሮች ተሞክሮ ያየነው ትንሽም ቢሆን የህግ ስርአት ያለበት ትንሽም ቢሆን የሰለጠነ መንግስት ያለበት ትንሽም ቢሆን ለአገር ደንታ ያለው መንግስት ያለበት ትንሽም ቢሆን ለታሪክ ትንሽ ደንታ ያለው መንግስት ያለበት በንደዚያ አይነት ሁኔታ አገር የሚባል ነገር መዳን አለበት ብሎ የማይስራው ነገር አለ ተብሎ የሚታመን ሃይል ባለበት ሁኔታ እነኛን ነግሮች መሞከር በርግጥም ውጤት ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ሊገመት ይችላል በኛ እምነት ይህ መንግስት ለምንም ለነኚህ ከፍተኛ እሴቶች አገር ለሚባል ነገር ፣ህዝብ ለሚባል ነገር ፣ ሰላም ለሚባል ነገር ቅንጣት ታክል ዴንታ የሌለው ማንንም ሰው በስልጣን ለመቆየት ብሎ ማንንም ሃይል አገርነ ጭምር ለማጥፋት ወድኋላ የማይመለስ ሃይል ባለበት ያ አይነት የትግል ስልት የሚሰራ ሳይሆን የበለጠ ብዙ ቀውስ ውስጥ አገርን የሚከት ነው ብዙ የሰው ህይወትን የሚያጠፋ ነው ብዙ የንብረት መውደም የሚያደርስ ነው ብለን ስለምናምን ነው ይሄን ነገር ባጭር ለመቅጨት ሊያመጣ የሚችለውን ፍጹም መቆሚያ የሌለው እዳ በኋላ የውደፊቱ ትውልድ እንዳየሸከም ለማድረግ ባጭር መቀጨት አለበት እና ያንን ለማድረግ የሚያስችለውን አቅም በሙሉ መጠቀም አለበት ወደሚለው የትግል ስልት የሄድነው ስለዚህ ያ ይሰራል እንሞክረው የሚሉትን እሰየው እሱን ሞክሩት ከሰራ እኛም ደስታውን አንችለውም ግን እንደማይሰራ እያውቅን ዝም ብለን እሱን አንጠብቅም በምንችለውም በሌላውም መንገድ እንገጥመዋለን ወደሚል ነው የሄድነው

**ቪኦዔ ፣** ዶር ብርሃኑ እርሶ በግለዎ በሰላማዊ ትግል አምነው ነው ቀስተዳመናን ይዘው የቅንጅት አባል የሆኑት እስኪ የቀድመው ነጥብ ላይ ልመልሰወት ያኔ ቅንጅት የውስጥ መናቆር ነበረበት ጥንካራ አልነበረም የሰላማዊው ትግሉንም ደግሞ ጥጉ አላደረሰውም የሚባል ትችት አለና እዛ ላይ አሳበዎን ይስጡኝ ቀደም ብሎ እርሶ በሰላማዊ ትግል ሽግግር ካልተደረገ የሚመጣውም መንግስት ትክክለኛ ስርአት አያሰፍንም ብለው ያመኑ ሰው ነበሩና ?

**ዶር ብርሃኑ፣** ልክ ነው በመጀመሪያ ቅንጅት የተጠቀመው የትግል ስልት ሰላማዊ ህጋዊ በመንግስት የህግ ከላላ ስር ህግ እለ ብሎ ህገ መንግስት አለ ብሎ አምኖ በተወሰነ ደርጃ ያም ይሰራል ብሎ እነኛን ተገን አድርጎ ነበር ሲንቀሳቀስ የነበርው ቤቶች እንዳው ትንሽም ቢሆን ለህሊናቸው የሚሰሩ ተቋሞች ይሆናሉ ተብሎ እስከ ታመነ ድረስ ያን ነገር እስከመጨረሻው እድል ሊሰጠው ይገባል ብሎ ቅንጅትም ሆነ እኔ የነበርኩበት ቀስተ ዳመናን ስናቋቁም ያቀዳዳ አለ የንን እንጠቀም ብለን ነው የገባነው ከማንም በላይ የኢትዮጵያን የዚያን ጊዜ እንቅስቃሴ የሚያውቅ ሰው ማንም ሰው ከማንም በላይ ጭራሽ የዋህ ነው ኢህአዴግ ምን እንደሆነ አያውቅም እስከምባል ድረስ በያንዳንዱ ከኢህአዴግ ጋር የተደረጉ ድርድሮች ውስጥ የተሳተፍኩ የኢህአዴግ ሰዎችን ዋና ዋና አመራር የሚባሉትን ግዴለም ጤነኞች ናችው በክፍት በጥላቻ መታየት የለባቸውም ቢያንስ ታሪካችውን የማደስ ፍላጎት አላቸው ብየ እምከራከርው እኔ ነበርኩ ከማንም በላይ ወደዚህ አሁን ወደደረስኩበት ደረጃ ለመድረስ እንደዚህ ቀላል ነገር አይደለም እነኚህ ሰዎች ድርድር ላይ ቁጭ ብየ አይቻቸዋለሁ ዛሬ አሁን አንድ ነገር ያሉትን ከስዓት እንደፈለገ መሸምጠጥ የሚችሉ ሆነው ነው ያገኘኋቸው እና ከነዚህ ጋር የሚደርግ ነገር እኮ በተወሰነ ድረጃ በዛኛው ሳይድ ትንሽ እንኳ አነስተኛ ጨዋነት አነስተኛ እንኳ የሞራል ለከት አለ ብሎ እኮ ሲታመን ነው እነኚህ ሰዎች እንደዛ አይነት ነገር የላቸውም እነኚህ ሰዎች እጁን ወደላይ አርጎ የቀረበን ህዝብን በጥይት ለመቁላት ወደ ኋላ ለማለት በፍጹም የማይችሉ ሰዎች ናችው እና እነኚህን ሰዎች እኔ ጠቅላላ ኢህአዴግንና ህወሃትን ማለቴም አይደለም እንዳው የተወሰኑ ይህንን አሁን በበላይነት እየመሩ ያሉት ጥቂት ሰዎች ስልጣናቸውን ለመልቀቅ ወይም ስልጣናቸውን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር በምንም አይነት የሚመለሱ አይደሉም ስለዚህ ነጻነቱን የሚፈልግ ሰው ወይ መታገል ነው ወይ በባርነት መገዛት ነው ያንን ደግሞ በባርነት መገዛት በምንም አይነት እኔም ሆንኩ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚቀበለው አይደለም ብዬ ነው የማምነው ለዚህ ነው ወደዚህኛው ስልት የሄድነው

**ቪኦዔ ፣** አብዩ ነጥብ ባለንበት ዘመን ጦርነት ያዋጣል ወይ? በተለይም በአፍሪቃ ቀንድ ካለው የጂኦ ፖለቲካ እውነታ ግንቦት 7 አስፈላጊ ከሆነ በጦርም ቢሆን ከስልጣን አወርድዋለሁ የሚለው ኢህአዴግ ደግሞ ከምራባውያን ጋራ የፀር ሽብር ሽሪክ ከመባሉ እንዲሁም ደግሞ አሁን ኢትዮጵያ ቋንቋን መሰረት ባደረገ የክልል ስርአት ስለምትተዳድር ወደባሰ የርስበርስ ጦርነት አያስገባም ወይ? እንግዲህ የታወቁ ጦርነት የሚያስከትላችው ጠንቆችም አሉ ኢኮኖሚውን ማራቆትና የመሳሰሉት ለዚህ ምንድነው መልሰዎ፤

**ዶር ብርሃኑ፣** ጦርነት ቀላል ነገር አይደለም ምንም ጥያቄ የለውም ሰላም ምርጫ ቢሆን በሰላም መኖርን የሚጠላ ሰው ያለ አይመስለኝም ምርጫው በባርነትና ዝም ብሎ በመኖር መካከል ከሆነ ከጥንት ጀምሮ በታሪክ ያየነው እዚህ ስልጣኔ የደረሱ ሀይሎች ሁሉ ከባርነት ይልቅ ተዋግቶ ነጻነትን ማግኘት ይሻላል ብለው ታግለው ነጻነታቸውን አግኝተው ነው ለዚህ ብልጽግናና ለዚህ ሰላም የደረሱት በዛሬ ዘመን በ2009 ዓ.ም እነ ሙጋቤ እንኳን የትም እንደማይደርሱ አውቀው ተደራድረው ስራታቸውን እገር ከማጥፋት ለመመለስ በሚሞክሩበት ጊዜ እነመለስ እና እነበረከት ይሄን አገር ለማጥፋት ሆን ብለው የተነሱ እስኪመስል ድረስ የሚወስዱት እርምጃ ዝም ብለን ልናየው አንችልም ከሚል የሚውሰድ እርምጃ ነው ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ መርጠን የምንወስደው እርምጃ እይደልም ተገደን ነው ሁለተኛው ምን አደጋ ሊመጣ ይችላል መጨረሻ ካነሳሸው አደጋ እንጀምር ህብረተሰቡ እርስ በርስ በዘውግ በብሄር ተከፋፍሎ ችግር ውስጥ ሊገባ ይችላል በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ስርአት ያልተበደለ ብሄረሰብ አለ እንዴ ? ያልተረገጠ ማንነቱን እስኪረሳ ድረስ እነሱ በመረጧቸው አፈ ጮሌዎች እንደፈለገ ሲደረግ ያልቆየ የህብረተሰብ ክፍል አለ እንዴ? ትግራይን ጨምሮ ነጻነቱን እጥቶ ተለጉሞ ያን ያህል አመት እንዳልታገለ ለነጻነት ብሎ ከደርግ እንዳልታገለ ነጻነት የሌለበት መቀመቅ ውስጥ ነው እነዚህ ሰዎች የከተቱት፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝበ ሁሉም ብሄረሰብ ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ የሚመጣው ለውጥ በማንም ብሄረሰብ ላይ እንዳላነጣጠረ በሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት መብቶቹን የግልም ሆነ የቡድን መብቶቹ ተከበረው የሚኖሩበትን መሆኑን እስካሳየ ድረስ እኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ እርስ በርስ መተላለቅ አይሄድም ብየ አምናለሁ እንደዚህ መንግስት ስው እርስ በርሱ እንዲጣላ እንዲጋደል ያልሞከረ እኮ መንግስት የለም ይሄን ሁሉ እምቢ ብሎ በሰላም የኖር ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሲመጣ ወደ እርስ በርስ መባላት ይሄዳል የሚለው እኔ በፍጹም ተራ ፕሮፖጋንዳ ውጤት ካልሆነ በቀር በምንም ዓይነት እንደዛ አይነት ነገር ይመጣል ብየ አላምንም የኢኮኖሚና ሌሎች ችግሮች ይፈጠራሉ የተባለው አሁን ያለው እኮ የድህነት ሁኔታ ሰው በተራ የሚበላበት አገር እኮ ነው እየሆን ያለነው ምን ተገኘ ተብሎ ነው ከዚህ የባሰ ነገር ይመጣል ተብሎ የሚፈራው? ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ካለፉት አገዛዞች የተማርነው ነገር ያለ ይመስለኛል ከሁን በኋላ ሌላ አገዛዝ አገራችን ውስጥ ሊኖር አይገባም አይፈቀድለትም ይሄ እስከሆን ድረስ ሁላችንም ወደፊት የምናየው መብት የተከበረባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እስከሆነች ድረስ የበለጠ የፍቅር ስሜት የበለጠ የመተባበር ስሜት በውስጣችን አድሮ ሁሌ ስንመኛት የነበረችው ለሁላችንም እኩል የሆነች የሁላችንም መብት የምታከብር ኢትዮጵያ የምትመጣበት ጊዜ እየቀረብ ያለ ይመስለኛልና እኔ የሚታየኝ ችግር አይደለም እኔ የሚታየኝ የነጻነት ስሜት የሚያየኝ የደስታ ስሜት የሚታየኝ ብሩህ ተስፋ ነው

ለኢትዮጵያ ችግር አይደለም የሚታየኝ ይሄን ስራት ማውደም ነው የመጀመሪያ እርምጃችን እሱን ደግሞ ማድረግ የሚያቅተን አይመስለኝም ኢትዮጵያውያን ከተባበርን።

**ቪዮዔ** ፤ ዶር ብርሃኑ ነጋ ግንቦት7 ኢትዮጵያ ውስጥ ድርጅታዊ መዋቅር አለው?

**ዶር ብርሃኑ**፤ አዎ በደንብ

**ቪዮዔ** ሊነግሩኝ ይውዳሉ ስለድርጅቱ?

**ዶር ብርሃኑ**፤ አልወድም በእንዲህ አይነት ሁኔታ አገር ውስጥ ስላለው ድርጅት ማውራት ብዙ ሰዎችን ችግር ውስጥ ሊከት የሚችል ነው በጥንቃቄ ካለፈው ከቅንጅት ተምረናል የምንለውም አባሎቻችንን ወደፊት አጋልጥን የምናደርገውን እንቅስቃሴ አይኖርም በጥንቃቄ ነው እየሰራን ያለነው በሁሉም ያገሪቱ ክፍል ድርጅታዊ መዋቅራችን በሰፊው እየዘረጋን ነው እና የሄ ነው ከዛ በላይ የምናደርጋችውን ስራዎች በሬዴዮ ውይይት በቪኦዔ የምንነጋገርው ነገር አይኖርም

**ቪዮዔ**፤ እንግዲህ በተያያዘ በመግለጫችሁ የምናይው ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር የምታደርጉት ትብብር ጥሩ አዝማሚያ እንዳሳየ ይጠቀሳል እና ከየትኞቹ ድርጅቶች ጋር እና በምን በምንድነው የምትተባበሩት

**ዶር ብርሃኑ**፤ እኛ ሁለት መሰረታዊ የስልት ሳይሆን ስትራቴጅካዊ የሆኑ ውሳኔ ላይ ደርሰን ነው ይሄን ድርጅት ያቋቋምነው አንድ ማንም ድርጅት በግሉ ብቻውን የተወሳሰበውን የኢትዮጵያ ችግር ይፈታል ብለን አናምንም ስለዚህ ሰፋ ያለ ብዙ ማህበረሰብ ያቀፈ የወደፊቷ ኢትዮጵያን የተሻለች መሆኗን የሚያውቁ ሃይሎች የተሰባሰቡበት የለውጥ ጊዜ ያስፈልጋል ብለን እናምናለን ይህ ግን መርህ አልቦ የሆነ ኢህአዴግ ጠላት ነውና እንሰባሰብ ከሚል ሳይሆን ሁለት መሰረታዊ መርሆዎች መጠበቅ አለባችው ብለን እናምናለን የመጀመሪያው ሁሉም በእንዲህ አይነት ትብብር ውስጥ የሚገባ ሃይል ከአሁን በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝብ የመረጠው መንግስት በስተቀር በምንም አይነት በምንም ስም የሚገዛ ሃይል ሊኖር እንድማይችልና እንደማይገባው መስማማት አለብን ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የመንግስት የስልጣን እርከን ድረስ ያሉ ሃይሎች በህዝብ ተመርጠው ብቻ ነው ካሁን በኋላ ኢትዮጵያን ሊያስተዳድሩ የሚችሉት በዚህ መጀመሪያ መስማማት አለባችው ሁለተኛ ፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ልዩነቶች ባንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ የተፈጠሩ ልዩነቶች መሆናቸው ታውቆ በዛ የፖለቲካ ማህበረሰብ ክልል ውስጥ መፈታት አለበት ብለን እናምናለን ያ የፖለቲካ ማህበረሰብ ደግሞ ኢትዮጵያ ሃገራችን ናት ስለዚህ የፖለቲካ ችግሮችን በኢትዮጵያ ጥላ ስር ለመፍታት የሚፈልጉ በኢትዮጵያ ውስጥ መፈጠር ያለበት ስርአት ዲሞክራሲያዊ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ ሃይሎች ከዛ ውጭ ያላችውን ልዩነት በምርጫ ጊዜ ለህዝብ አቅርበው ለመፍታት እስከወሰኑ ድረስ ተባብረው ይሄን መንግስት ለመጣል ትጋግዘው ማውረድ አለባችው የሚል እምነት አለን እንደነኚያ ካሉ ሀይሎች ጋር ይህንን መሰረታዊ እምነታችንን ፊትለፊት አስቀምጠን ይሄን ሊያደርጉ ከሚችሉ ሃይሎች ጋር እየተነጋገርን ነው በመሰረታዊ የእምነት ደረጃ አብዛኞቹ ድርጅቶች ጋር ስምምነት አለን ዝርዝር ነገሮችን ቀስ እያልን እየሰራን እናበለጽገዋለን ብለን እናምናለን ያ ትብብር ተግባራዊ ይሆናል ብለን እናምናለን

**ቪዮዔ** ፤ የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች በልዩ ልዩ ስም ተከፋፍለው አሁን እርሶም ከሚመሩን ግንቦት 7 ጭምር አንድ 5 ወይንም 7 የሚደርሱ ድርጅቶች እንደየድርጅቱ ሰው አመለካከት ማለት ነው በተቃዋሚ ጎራ ናችሁ እና ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ፖሊሲ ላይ የጋራ አቋም ካላችሁ በአነስተኛ ፕሮግራም ተባብራችሁ መቀጠል እንዴት አልተቻለም ይችን የመለሱልኝና እናጠቃልላለን

**ዶር ብርሃኑ**፤ በመጀመሪያ ጥያቄው ትክክል አይመስለኝም 7 አሉ የተባሉት እነማን እንደሁኑ አላውቅም ኢህአዴግ የፈጠራችውን ጨምረሽ ከሆን እነሱን ለምን ቅንጅት እንደምትሏችው ምናልባት የዘገባ ግዴታ ሆኖባችሁ ነው መሰለኝ እንጂ በመሰረቱ ቅንጅት ተከፋፈለ ከተባለ ሁለት ቦታ ነው የተከፈለው በቀድሞው የቅንጅት መሰረታዊ እምነቶች ላይ ተመስርቶ መስረታዊ እምነቶች ስል ባጠቃላይ የፖለቲካ መርሆዎች ብቻ ሳይሆን የትግል ስልትንም በሚመለከት ሰላማዊና ህጋዊ ትግል እናደርጋለን ብሎ የሚያምነው የቅንጅት ሃይል የተከፈለው ሁለት ቦታ ነው እሱም መከፈልም መባሉን እጠራጠራለሁ በናቶ ሃይሉ በኩልም ያሉት ሰዎች ወደ ድሮ ድርጅታችን እንመለሳለን ብለው ይሄን ሁሉ ትርምስ የፈጠሩት እነሱ ናችው ወደዛ መጥተዋል ከዛ ውጭ ያለው ሃይል ከበፊት መኢአድ ኢዳፓመድንም ቀስተ ዳመናም በኢዴሊም የነበሩት ተሰባስበው ያው የድርጅት ስማችውን በነኚህ አይን አውጣ መንግስት በጉልበት ከተቀማ በኋላ ያንን የቀድሞውን የትግል ስትራቴጂ እንቀጥልበታለን ብለው አንድነት የሚባለውን ድርጅት መስርተዋል እነኚህ ሁለቱ ናቸው እኛ ከቅንጅት ከፍለን የፈጠርነው ድርጅት የለም እኛ ቅንጅት ይባል ከነበርው ደርጅት በመሰረታዊ የትግል ስልት ደርጃ ስንለይ እንደ ቅንጅት ሆነን አንድ ሌላ አካል ሆነን አይደለም የወጣነው እኛ ከቅንጅት ለቀናል ብለን ድርጅቱን መልቀቃችን ተናግረን ነው የለቀቅነው ስለዚህ እኛ ሌላ የቅንጅት አካል አልፈጠርንም እኛ ከዚህ በፊት ቅንጅንት ስብስብ ውስጥ ያልነበሩም አሁን ባዲስ ደረጃ በቀየስነው የትግል ስልት ውስጥ መሳተፍ የሚፈልጉ የተለያዩ ሀይሎች አንድ ላይ ሁነን በኋላ ላይ ግንቦንት 7ን የመሰረትነው ስለዚህ ግንቦት 7 የቅንጅት ክፍፍል ውጤት ተደርጎ የሚቀርበው በፍጹም ስህተት ነው ያንን የትግል ስልት አንቀበልም ብለን የወጣን ሰዎች ነን እና ሌላ ድርጅት ነው ያቋምነው

**ቪዮዔ** ፤የግንቦት 7 የፍትህ የንጻነትና የዲሞክራሲ ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ባድማጮች ስም አመሰግናለሁ

**ዶር ብርሃኑ**፤ በጣም አመሰግናለሁ

## የአድዋ ድልን …. (ከገጽ 1 የዞረ)

ነገር ግን ከዚያው ታፍኖ ቀረ አልተመለሰም፤ ጀነራል አሪሞንዲን የመሰለ ጀግና ከብዙ መኳንንት ጋራ ከዚያው ወድቆ ቀረ ። አልቤርቶኔን የመሰለ ብርቱ ጀነራል፤ ከብዙ ጀግና ጋር፤ ከመሃል ታፍኖ ቀረና ተማረከ ። …በቀረውስ ምን ሊሆን፤ ምንና ምን፤ የሸዋ ፈረሰኛ፤ የጎጃም እግረኛ፤ የትግሬ ነፍጠኛ፤ ያማራ ስልተኛ ከቦ፤ ያናፋው ይቆላው ያንደገድገው ጀመር ።የኢጣልያው ጦር አለቃ ጀነራል ባራቴሪ ነገሩን ባየ ጊዜ…በፈረስ ተጋብቶ ወደኋላው ተሸመጠጠ ። ያ ሁሉ አላበሳው የመጣ የኢጣልያ ጀግና አለስፍራው ገብቶ፤ አለፈረስ አለ ምን፤ በዚያ ጠጠር በዚአ ቁልቁለት፤ በዚያ ጠባብ መንገድ እንዴት አድርጎ በከባድ መጫሚአ እሩጦ ያምልጥ? እንዲአው ብቻ፤ ከንዝርት የቀለለ የጁዬ፤ ተነብር የፈጠነ በጌምድሬ፤ ተቋንጣ የደረቀ ትግሬ፤ እየደረሰ ፈጀው፤ አሰጣው፤ ዘለሰው ። …የጀነራል ባራቴሪን መሸሽና፤ የጦሩን መፈታት ባየ ጊዜ፤ ያ ሁሉ ወደኋላ የነበረ መድፈኛ፤ መጫኛውን በጎራዴ እየቆረጠ፤ መደፉን እየጣለ፤ በመድፉ ስፍራ እሱ እየተተካ፤ ባጋሰሱ እየጋለበ አስመራውን ገባ ። ካንድ ላይ ብቻ፤ አስራ ስምንት መድፍ አንድ ጊዜ ሳይተኮስ፤ እስከ ጥይቱ እስከ መንኮራኩሩ ወድቆ ቀርቶ ተያዘ ። …አጤ ምኒልክ፤ ያን ሁሉ መድፍ፤ ያን ሁሉ ነፍጥ፤ አጋፈው ይዘው፤ ያን ሁሉ ምርኮኛ በፊት እየነዱ፤ ፊት ያዲግራትን ምሽግ ሰብረው፤ ቀጥለው ወደ መረብ ለመቆልቆልና አስመራ ያለውን ጦር እስከ ባህር ለማባረር አሰቡ ። ኋላ ግን ሰራዊትዎ ሁሉ ሶስት ወር ሙሉ ትግሬ ላይ በርሃብ ተጎድቶ ነበረና፤ ከርሞ ለመመለስ ወደሸዋ ተመለሱ ።"

ከመቶ አመት በፊት ለህትመት የበቃው መፅሃፍ ምስክርነት ይህ ነው ። ይህ የኢትዮጵያውያን መኩሪያ መጎናፀፊያ የሆነውን የአድዋ ድል፤ በክህደት የታጀለው ወያኔ "የትግራይ ድህነት የጀመረበትና፤ የሸዋ የበላይነት የተረጋገጠበት "ዘመነ ሸ" ብሎ በክህደት ታሪኩ መዝገብ ውስጥ አካቶታል ። ዛሬ ላለንበት መቀመቅ አንዱ ምክንያት፤ በድል ታሪካቸው የሚያፍሩ፤ ወይም ለጊዜያዊ የስልጣን ጥማቸው እንዲመች፤ የክለሳ ታሪክ ለመፃፍ የቆረጡ ከሃዲ ሃይሎች በትረ ስልጣኑን የጨበጡ የመሆኑ ሃቅ ነው ። ለአድዋ ድል ያላቸውን ጥላቻ ለመግለፅም፤ የዛሬ 13 አመት የድሉ 100ኛ አመት ሲከበር፤ "የጨለንቆ ፍጅት" 100ኛ አመት የሚል በአል ፈጥረውና የተረሳን የታሪክ ጠባሳ እንደ አዲስ አምግለው ድላችንን በፍጅት ታሪክ ለማኮሰስ ወይነው የነበረው ። አድዋ ራሷ እንዲህ አይነት ከሃዲዎች ከእቅፏ በመውጣታቸው ማህፀኗን ሳትረግም አልቀረችም ማለት ማጋነን አይመስለኝም ።

ሌላው ዛሬ ላለንበት ችግር መንስኤ፤ በአድዋ ድል ማግስት፤ ቅድም አያቶቻችን አውሮፓ የጦር መሳሪያና የመጓጓዣ ቴክኖሎጂን ያዳበረችበትን ምስጢር ለመረዳት ባደረጉት ምርምር፤ የዘመናዊ ትምህርት አስፈላጊነት ላይ በመስማማታቸው፤ ምእራብ ጠቀስ ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ በወሰዱት እርምጃ፤ በጦር ሜዳ ድባቅ የመቱትን የአውሮፓ ቅኝ አገዛዝ፤ በስርአተ ትምህርቱ አማካይነት ሊረቱበት የመቻሉ ጉዳይ ነው ። በዘመናዊ ትምህርት ስም በታሪኩ የሚያፍር፤ ማንነቱን የማያውቅ፤ ለፈረንጅ አዳሪ፤ ለፈረንጅ አቀባይ የሆነ፤ በፈረንጆች 'ሰልጥኖ' በፈረንጆች የታጠቀ ትውልድ መፈጠሩና፤ በበላይነት ከሚያያቸው ባዕዳን እርጥባን ከመለመን ውጪ፤ ሃገሪቷ በውስጣዊ አቅሟ ራሷን ችላ መቆም ትችላለች ብሎ በራሱ የሚመካ ትውልድ የተመናመነ መሆኗና፤ ለከተማ ህይወት የተጋለጠው ሁሉ ስደትንና ዲቪ ሎተሪን እንደ ህይወቱ መታደጊያና ህልሙ የሚያይ መሆኑ ሌላው ላለንበት ፅልመት የወረወረን ጉዳይ ነው ።

ዛሬ የአድዋ ድልን 113ኛ አመት ስንዘክር፤ ቅድም አያቶቻችን እንዴት ወታደሩ ባላገሩን እንዳድቦለቦለው ጭቃ መጠፍጠፉን አቁሞ ለህግና ስርአት ተገዢ ለማድረግ እንደቻሉና፤ ምንስ ብናደርግ መልሰን የወያኔ ነፍጠኞች እንደ እንጨታቸው እንዲጠርቡን እንደፈቀድንላቸው፤ የገባንበትን መቀመቅ አይተን፤ ለህግ የበላይነት የምናደርገውን ትግል ለማጧጧፍ ትምህርት ልንቀስምበት ይገባል ። የታሪክ ጥቅሙ ይሄው ነው ። ወደ ኋላ ተመልክተን፤ ከበጎ ፍፃሜዎቻችንም ሆነ ውድቀታችን ትምህርት ለመገብየት የመቻላችን ሃቅ ። ከአድዋ ድል የምንማረው ደግሞ ትልቅነትን፤ ሆደ ሰፊነትን፤ አርቆ ማስተዋልን፤ በራስ መተማመንን፤ ራስን ማክበርን ነው ። በተለይ ዛሬ አለም በጥልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ በተዋጠችበት ወቅት፤ እነዚህ ከአድዋ አውድማ የተማርናቸው እሴቶች ረጅም እርቀት ይዘውን ሊሄዱ የሚችሉ መወንጨፊያዎቻችን ናቸው ።

**ዘለአለማዊ ዝክር ለአድዋ ጀግኖች !**

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org

# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።